22100014

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

**AMHARIC A1 – HIGHER LEVEL – PAPER 2**
**AMHARIQUE A1 – NIVEAU SUPÉRIEUR – ÉPREUVE 2**
**AMHÁRICO A1 – NIVEL SUPERIOR – PRUEBA 2**

Friday 14 May 2010 (morning)
Vendredi 14 mai 2010 (matin)
Viernes 14 de mayo de 2010 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

INSTRUCTIONS TO CANDIDATES

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied. You may include in your answer a discussion of a Part 2 work of the same genre if relevant. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.

INSTRUCTIONS DESTINÉES AUX CANDIDATS

- N'ouvrez pas cette épreuve avant d'y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. Vous devez baser votre réponse sur au moins deux des œuvres de la 3e partie que vous avez étudiées. Le cas échéant, vous pouvez inclure dans votre réponse une discussion sur une œuvre du même genre littéraire étudiée dans la 2e partie du programme. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la 3e partie n'obtiendront pas une note élevée.
- Vous n'êtes pas autorisé(e) à amener des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d'examen.

INSTRUCCIONES PARA LOS ALUMNOS

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Elija un tema de redacción. Su respuesta deberá basarse en al menos dos de las obras estudiadas en la Parte 3. Se podrán hacer comentarios sobre una obra de la Parte 2 del mismo género, si fuera necesario. Las respuestas que no incluyan una discusión sobre al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán notas altas.
- No se permite traer a la sala de examen copias de las obras estudiadas.




© International Baccalaureate Organization 2010

https://xtremepape.rs/

*ከሚከተሉት በአንዱ ላይ ሀተታ ፃፍ(ፃፊ)፡፡ መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ መመስረት አለበት፡፡ በክፍል ሁለት ስር ከሚገኝ አንድ ተመሳሳይ የስነጽሁፍ ዘርፍ ማጣቀሻ ማስገባት ይፈቀዳል፡፡ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ ያልተመሰረተ መልስ ከፍተኛ ነጥብ አያስገኝም፡፡*

**ድራማ**

**1.** አንድ ፀሀፊ ተውኔት የተዋጣለት ስራ ሰራ የሚባለው ተዋናዩ ህይወት የሚሰጠው ገፀባህሪ መፍጠር ሲችል ነው፡፡ ያጠናሃቸውን የተለያዩ ፀሀፊ ተውኔቶች ሁለት ድራማዎች ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ሀሳብህን አስረዳ፡፡

**2.** የድራማ ትልም (ፕሎት) የሚመሰረተው በምልልስ ሲሆን ውጤታማነቱም የሚወሰነው በምልልሱ ይዘትና በተዋንያኑ ችሎታ ነው፡፡ የዚህን ሃሳብ ትክክለኛነት ያጠናሃቸውን የተለያዩ ፀሀፊ ተውኔቶች ሁለት ድራማዎች ምልልሶች በመመርኮዝ ግለጽ፡፡

**ረጅም ልቦለድ**

**3.** የረጅም ልቦለድ ግጭት በገፀባህሪው አእምሮ ውስጥ ወይም በገፀባህርያት መካከል ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህ አይነቱ ግጭት የሚታይበትን ሁኔታ ያነበብካቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር የአረፍተነገሩን ትክክለኛነት አስረዳ፡፡

**4.** የረጅም ልቦለድ መቼት በልቦለዱ የሚከናወኑ ድርጊቶች እውነተኛ እንዲመስሉ ያደርጋል ወይም በተቃራኒው ድርጊቶችን የማይታመኑ ለማድረግ ደራሲው ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ባጠናሀቸው የተለያዩ ደራስያን ሁለት ስራዋች ውስጥ ይህ ሁኔታ እንደምን እንደቀረበ አስረዳ፡፡

**ስነግጥም**

**5.** ገጣምያን ስሜትን ለመኮርኮርና የአንባቢውን ትኩረት ለመሳብ ምስል ከሳች ቃላት ይጠቀማሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ ያነበብካቸውን የተለያዩ ገጣምያን ቢያንስ ሁለት ግጥሞች በመጥቀስ አብራራ፡፡

**6.** የቃላት ንጽጽር፣ ተለዋጭ ዘይቤ፣ ተምሳሌትና የቃላት ድግግሞሽ የሚታይበት ስነልሳናዊ አወቃቀር ግጥምን ለመረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ ያነበብካቸውን የተለያዩ ገጣምያን ቢያንስ ሁለት ግጥሞች በመጥቀስ አብራራ፡፡



https://xtremepape.rs/

**ዝርው (ከረጅምና አጭር ልቦለድ ሌላ)**

**7.** የዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) ፀሀፊ የሚፈልገውን ሀሳብ የሚያስተላልፈው በሚያስቀምጠው ሀሳብ ብቻ ሳይሆን ሀሳቡን በማያቀርብበት መንገድም ጭምር ነው፡፡ ያጠናሃቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማወዳደር የሀሳቡን ጠቀሜታ አስረዳ፡፡

**8.** የዝርው ጽሁፍ (ለምሳሌም ወግ) ፀሃፊ አንድ ሃሳብ ካቀረበ በሁዋላ ሀሳቡን በማስረጃ አስደግፎ ማስረዳት አለበት፡፡ ይህንን አረፍተ ነገር ያጠናሃቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በመጥቀስ ግለጽ፡፡

**አጭር ልቦለድ**

**9.** አጭር ልቦለድ የተዋጣለት ነው የሚባለው በአጨራረሱ ነው፡፡ በዚህ ሀሳብ ምን ያህል ትስማማለህ? የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር ሀሳብህን ግለጽ፡፡

**10.** በአጭር ልቦለድ ገፀባህርያት ተአማኒ የሚሆኑት ወጥና በገሀዱ አለም ያሉ ሰዎችን መስለው ሲቀርቡ ነው፡፡ ይህንን ሃሳብ የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አስረዳ፡፡

**ሁለገብ (አጠቃላይ)**

**11.** ስነጽሁፍ ሰብእናችን እንዲዳብርና አስተሳሰባችንም እንዲጎብት የማድረግ ሃይል አለው፡፡ ይህንን ሃሳብ የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አስረዳ፡፡

**12.** ደራስያን አስቂኝ አጋጣሚዎችን ፣ ሁኔታዎችንና ባህርያትን በማቅረብ አንባቢውን ፈገግ ያሰኛሉ፡፡ ይህንን ሃሳብ የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በምሳሌነት በማወዳደር አብራራ፡፡

**13.** ስነጽሁፍ ባህላችንንና ታሪካችንን ለመረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ያነበብካቸውን የተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በመጥቀስ ይህንን ሃሳብ አስረዳ፡፡

**14.** ስነጽሁፍ ደስ ከማሰኘት በተጨማሪ አስተማሪ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህንን ሃሳብ በተለያዩ ደራስያን ቢያንስ ሁለት ስራዎች ምሳሌነት አብራራ፡፡



https://xtremepape.rs/